# ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል

## ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# በግዙፍ ኢኮኖሚ ውስጥ የሚመራ ጤናማ የፋይናንስ ሥርዓት

ውድ አንባቢያን! ባለፈው ሳምንት እትማችን የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል የፋይናንስ ሥራ ዘርፍ በተቋሙ ከሚንቀሳቀሰው ከፍተኛ ኢኮኖሚ እና ከውጤታማ ክንውኖቹ ጀርባ ያለውን ሚና በተመለከተ የዘርፉ የሥራ ኃላፊ አቶ ደመረ አሰፋ የሰጡንን ከፊል መረጃ አስነብበናችሁ እንደነበር ይታወሳል። በዛሬው እትማችንም ቀሪዎቹን መረጃዎች እንደሚከተለው አጠናቅረን አቅርበንላችኋል።

አቶ ደመረ እንደሚገልጹት፤ ተቋሙ በአሁኑ ሰዓት ስድስት መቶ ቢሊዮን ብር የሚገመት ቋሚ (ፊክስድ) ሀብት ያስተዳድራል። ይህ ግዙፍ ኢኮኖሚ ጤናማ በሆነ የፋይናንስ ሥርዓት የሚመራ በመሆኑ ባለፉት አራት ተከታታይ ዓመታት ከኦዲት ግኝት የጸዳ ውጤት ታይቶበታል።

ባለፉት አራት ተከታታይ ዓመታት ከኦዲት ግኝት የጸዳ ውጤት ሊመዘገብ የቻለው ተቋሙ ይህንን ሀብት በተገቢው ሁኔታ ማስተዳደርና ለኦዲት ሥርዓቱ ምቹ የፋይናንስ ሰነዶችን ማመቻቸት በመቻሉ እንደሆነ ገልጸዋል። የሂሳብ መረጃዎችን አደራጅቶ መያዝ ፣ መረጃዎቹን በኮምፒዩተር ሲስተም ውስጥ ማስገባት፣ ሲስተም ላይ የተቀመጠውን መረጃ በሀርድ ኮፒ አደራጅቶ መረጃውን ለሚፈልግ ሶስተኛ አካል ማቅረብ፣ የብድርም ሆነ የክፍያ ሥርዓቶችን በስምምነቱ መሰረት ወቅቱን ጠብቀው እንዲፈጸሙ ማድረግ ለፋይናንስ ሥርዓቱ ውጤታማነት አስተዋጽኦ ካበረከቱ ጉዳዮች ውስጥ የሚጠቀሱ ናቸው።

የተቋሙን አጠቃላይ የሀብት መጠን አውቆ ተስማሚ የአሠራር ሥርዓቶችን መቅረጽ የተቋሙ ተቀዳሚ ተግባር ነበር። በመሆኑም የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ቀደም ሲል የነበረውን ሀብቱን በተገቢው ደረጃ ለማወቅ



አቶ ደመረ አሰፋ

አማካሪ ድርጅት በመያዝ ነባሩን አሠራር በመተው ወደ IFRS « International finance reporting system » መሸጋገርን መርጧል።

ሁሉም የተቋሙ የሥራ ዘርፎች ከፋይናንስ ጋር የተገናኙ ሥራዎቻቸውን ወጥ በሆነ መንገድ በመሥራታቸው ውጤት ተገኝቷል። ውጤቱ የሂሳብ ክፍል ሠራተኞች ድርሻ ብቻ ሳይሆን ከዋና ሥራ አስፈጻሚው እስከታችኛው ፕሮጀክት ሠራተኛ ድረስ ተገቢውን የፋይናንስ የአሠራር ሥርዓት በመፈጸማቸው የተገኘ ነው።

ተቋሙ ከተለያዩ አማራጮች ገቢ ያገኛል። የተቋሙ ዋና ደንበኛ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል እንደመሆኑና እርሱም የመንግሥት ተቋም በመሆኑ በገቢ አሰባሰብ ላይ የጎላ ችግር አይከሰትም። አንዳንድ ጊዜ በአገር ውስጥ እና በውጭ ደንበኞች ጥቂት የሚባል መጓተት ቢኖርም ተቋሙ አገልግሎት ሰጥቶ መቀበል እየተገባው ሳይቀበል የቀረው ገቢ የለም። ይህም የተቋሙ የፋይናንስ ዘርፍ እንዱ ስኬት ነው።

የተቋሙ የገቢ አቅም ከዓመት ወደ ዓመት እያደገ መጥቷል። ለዚህም ምክንያቱ መንግሥት ለዘርፉ ትኩረት መስጠቱን ተከትሎ ተቋሙ ኃይል እያመረተ የመሸጥ አቅሙ በማደጉ ነው። የተቋሙ ሥራዎች በአብዛኛው የውጭ ምንዛሪ የሚጠይቁ እንደመሆናቸው ብሄራዊ ባንክ ቅድሚያ ከሚሰጣቸው እና ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ከሚመድብላቸው ተቋማት አንዱ ነው። ኤክስፖርት ከሚያደርገው ኃይል የሚያገኘውን የውጭ ምንዛሪ መቶ በመቶ ለግብዓት መግዣ እንዲጠቀምበት መንግሥት ፈቅዶለታል። ተቋሙ በሚያገኘው የውጭ ምንዛሪ ለግብዓት የሚያገለግሉ ግዢዎችን በመፈጸም ኢንቨስትመንቱን እያስፋፋ ጎን ለጎን ገቢውን ያሳድጋል ብለውናል።

ኃይል ተመርቶ መዳረሻ ቦታ ከሌለው ይባክናል ያሉት አቶ ደመረ፤ በተለይም የኃይድሮ ኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ግድቦች ሲገነቡ የሚያዘው ውሃ በፍጥነት ኃይል እንዲያመነጭ ጥቅም ላይ ካልዋለ በቀጣይ የሚመጣውን ውሃ መያዝ አይቻልም። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በመንግሥት ከፍተኛ ድጋፍ የማከፋፈያ ጣቢያዎችን በመገንባትና እና የማሰራጫ መስመሮችን በመዘርጋት የኃይል መዳረሻዎችን ማስፋት ተችሏል። የኤክስፖርት መጠን እያደገ መምጣቱም የገቢውን መጠን እንዲጨምር አድርጎታል። በተለይም በቅርብ ጊዜ የኢትዮ-ኬንያ የኃይል ማስተላለፊ መስመር ዝርጋታ ተጠናቆ ሥራ መጀመሩ የተቋሙን የገቢ አቅም አሳድጎታል።

የተቋሙ ገቢ ከዓመት ወደ ዓመት እያደገና በአገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ የሚጫወተው ከፍተኛ ሚና እየጨመረ ቢመጣም ዘርፉ ከሚጠበቅበት የገቢ መጠን አንጻር ገና ብዙ መሥራት እንደሚጠበቅበት ተናግረዋል። ተቋሙ ከዓለም ባንክና ከአፍሪካ ልማት ባንክ እየተበደረ የኤሌክትሪክ መሰረት ልማት ግንባታዎችን በማስፋፋት ላይ ይገኛል። ብድሩን ለመክፈል ደግሞ የገቢ አቅሙን ማሳደግ ይጠበቅበታል።

የዶላር ምንዛሪ እየጨመረ መሄድ በተቋሙ የብድር አከፋፈል ሥርዓት ላይ ተጽዕኖ እያሳደረ መሆኑን አቶ ደመረ ተናግረዋል። በውጭ ምንዛሬ የተገኘው ብድር በየዓመቱ ራሱን ችሎ ትርፍና ኪሳራው ይሰላል። የብድር ስምምነቱ በተፈጸመ ጊዜ አንድ የአሜሪካ ዶላር ይመነዘር የነበረበት የብር መጠን አሁን ካለው ምንዛሪ አንጻር ከፍተኛ ልዩነት አለው። ይህ ክስተት በተቋሙ የብድር አከፋፈል ሥርዓት ላይ ትልቅ ጫና ያሳድራል። እንዲህ አይነቱን ችግር ለመቋቋም የኤክስፖርትም ይሁን የሀገር ውስጥ አቅርቦትን ማሳደግና የሽያጭ ታሪፍን ማሻሻል እንደሚያስፈልግ ገልጸዋል። ብድርን ለመክፈል ብቻ ሳይሆን ቀጣይ ኢንቨስትመንቶችንም ለማስፋፋት ተቋሙ ከራሱ ገቢ መጠቀም የሚያስችለውን አቅም እንዲፈጥር ለማድረግ የተቋሙ ማኔጅመንት ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ ይገኛል ብለዋል።

በአሁኑ ሰዓት እየተገነቡ ካሉት የታላቁ ሕዳሴ እና የኮይሻ ሃይድሮ ኤሌክትሪክ ማመንጫ ግድቦች በስተቀር አብዛኛዎቹ የማከፋፈያ ጣቢያዎችና የማስተላለፊያ መስመሮች ግንባታ ተቋሙ በራሱ የፋይናንስ አቅም እያከናወናቸው የሚገኙ መሆናቸውንም ጠቅሰዋል።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል የኢኮኖሚው አንቀሳቃሽ ሞተር በመሆን የአገሪቱን ትንሳኤ ያረጋግጣል ተብሎ ተስፋ የተጣለበት ተቋሙ ነው። የፋይናነስ አሠራሩን በማዘመን የሚያንቀሳቅሰውን ከፍተኛ ኢኮኖሚ በአግባቡ እያስተዳደረ ከአንዱ የእድገት ምዕራፍ ወደሚቀጥለው የእድገት ምዕራፍ በመሸጋገር ላይ ይገኛል። ይህን ስኬቱን አጠናክሮ በመቀጠል ያሰበው ግብ ላይ እንዲደርስ የተቋሙ ሠራተኞች በሙሉ በትብብር መንፈስ የመሥራት ልምዳቸውን እንዲገፉበት አቶ ደመረ አሳስበዋል።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል